# የግላዊነት አሠራሮች ማስታወቂያ

## የአደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀም ችግር የሕክምና ፕሮግራሞች

**ግላዊነትዎን ለመጠበቅ ቁርጠኞች ነን**

የፌዴራል ሕግ የአደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀም ችግር ያለባቸውን ታካሚዎች መዛግብት ሚስጥራዊነት ይጠብቃል።

ይህ ማስታወቂያ የሚከተሉትን ይገልጻል፦

- ስለ እርስዎ የሚገልጽ የጤና መረጃ እንዴት ጥቅም ላይ ሊውል እና ይፋ ሊደረግ እንደሚችል
- ከጤና መረጃዎ ጋር በተያያዘ ያለዎት መብቶች
- የጤና መረጃዎ ግላዊነት ወይም ደህንነት ሲጣስ፣ ወይም ከመረጃዎ ጋር በተያያዘ ያሉ መብቶችዎ ሲገደቡ እንዴት ቅሬታ ማቅረብ እንደሚችሉ

የዚህን ማስታወቂያ ቅጂ (በወረቀት ወይም በኤሌክትሮኒክስ ቅጽ) የማግኘት እና ማንኛውም ጥያቄ ካለዎት ከCOREWELL HEALTH ግላዊነት ቢሮ ጋር በ**616.486.4113** ወይም **privacy@corewellhealth.org** የመወያየት መብት አለዎት።

በCorewell Health ውስጥ የጤና መረጃዎ ግላዊነት ሁልጊዜም ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው። ይህ ማስታወቂያ ለCorewell Health የአደንዛዥ ዕፅ ወይም የአልኮል ሱሰኝነት (substance use disorder) ታካሚዎች ስለ ግላዊነት መብቶቻቸው እና Corewell Health እነዚህን መብቶች ለመጠበቅ ስላለው ቀጣይነት ያለው ቁርጠኝነት መረጃ ይሰጣል። የጤና መረጃዎ በሚሰበሰብበት እና ጥቅም ላይ በሚውልበት መንገድ ላይ ምርጫዎችን የማድረግ መብት አለዎት።

**የግላዊነት አሰራሮች ማስታወቂያ**

ይህ ማስታወቂያ ስለ እርስዎ የአደንዛዥ ዕፅ ወይም የአልኮል ሱሰኝነት ሕክምና መረጃ እንዴት ጥቅም ላይ ሊውል እና ሊገለጽ እንደሚችል፣ እንዲሁም ይህን መረጃ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ይገልጻል። ይህ ማስታወቂያ ወደ አደንዛዥ ዕፅ ወይም የአልኮል ሱሰኝነት ፕሮግራም በሚገቡበት ጊዜ ይሰጥዎታል፤ ወይም በወቅቱ በነበሩበት የጤና ሁኔታ ምክንያት ለመረዳት የማይችሉ ከሆነ፣ መረዳት በሚችሉበት ጊዜ ወዲያውኑ ይሰጥዎታል። **እባክዎ ይህንን ማስታወቂያ በጥንቃቄ ያንብቡ።** ይህ ማስታወቂያ ከፌብሩዋሪ 16፣ 2026 ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

**ይህ ማስታወቂያ በማን ላይ ተፈጻሚ ይሆናል**

ይህ ማስታወቂያ በፌዴራል ሕግ 42 CFR የክፍል 2 (የክፍል 2) መሠረት የአደንዛዥ ዕፅ ወይም የአልኮል ሱሰኝነት ሕክምና ወይም አገልግሎቶችን በሚሰጡ የCorewell Health ፕሮግራሞች ወይም አቅራቢዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል። በዚህ የግላዊነት አሠራሮች ማስታወቂያ ላይ የሚደረጉ ማናቸውም ለውጦች፣ ሕክምና በሚያገኙበት ቢሮ ወይም ተቋም፣ ወደ **616.486.4113** በመደወል ወይም ወደ **privacy@corewellhealth.org** ኢሜይል በመላክ ማግኘት ይችላሉ።

**የጤና መረጃዎን በተመለከተ ያለን ቃል ኪዳን**

የጤና መረጃዎ የግልዎ እንደሆነ የምንገነዘብ በመሆኑ የመረጃውን ግላዊነት ለመጠበቅ እንተጋለን። የምንጠቀምበት፣ የምናመነጨው፣ የምንይዘው እና የምንገልጸው ስለ እርስዎ የሚገልጽ የጤና መረጃ፣ ከእኛ እና ከ የክፍል 2 ፕሮግራሞቻችን ከሚያገኙት የአካል እና የአእምሮ ጤና እንክብካቤ ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል። ከCorewell Health ለሚያገኟቸው እንክብካቤዎች እና አገልግሎቶች መዝገብ እናዘጋጃለን። ይህ መዝገብ ለእርስዎ ጥራቱን የጠበቀ እንክብካቤ እንድናቀርብ እና የተወሰኑ የህግ መስፈርቶችን እንድናከብር ያስችለናል። ይህ ማስታወቂያ በCorewell Health በሚያዙ በኤሌክትሮኒክም ሆነ በወረቀት እና ከእርስዎ እንክብካቤ ጋር በተያያዙ የክፍል 2 መዛግብት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል። እንክብካቤ የሚሰጥዎት ዶክተር የCorewell Health ቡድን አባል ካልሆኑ፣ የሕክምና መረጃዎን አጠቃቀም እና ይፋ ማድረግን በተመለከተ የተለያዩ ፖሊሲዎች ወይም ማስታወቂያዎች ሊኖራቸው ይችላል። ይህ ማስታወቂያ የክፍል 2 የጤና መረጃዎ እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል ወይም ይፋ እንደሚደረግ ይነግርዎታል። እንዲሁም የአደገኛ ዕፅ አጠቃቀም ችግር የጤና መረጃን አጠቃቀም እና ይፋ ማድረግን በተመለከተ የእርስዎን መብቶች እና ግዴታዎች ይገልፃል።

የሚከተለውን ለማድረግ በህግ እንገደዳለን፦

- የእርስዎን ጥበቃ የሚደረግለት የጤና መረጃ (Protected Health Information - PHI) — የእርስዎን የክፍል 2 ጤና መረጃ ጨምሮ — ግላዊነት እና ደህንነት መጠበቅ።
- ስለ ሕጋዊ ግዴታዎቻችን እና የክፍል 2 መዛግብትን በተመለከተ ስለምንከተላቸው የግላዊነት አሠራሮች ለታካሚዎች ማስታወቂያ መስጠት።
- በአሁኑ ወቅት በሥራ ላይ ባለው ማስታወቂያ ላይ የተገለጹትን የግላዊነት አሠራሮች መከተል።
- ሲጠይቁ የዚህን ማስታወቂያ ቅጂ መስጠት።
- ደህንነቱ ባልተጠበቀ እና ጥበቃ በሚደረግለት የጤና መረጃ ላይ — የአደንዛዥ ዕፅ ወይም የአልኮል ሱሰኝነት መረጃን ጨምሮ — የመረጃ ጥሰት ሲያጋጥም ጉዳቱ የሚመለከታቸውን ግለሰቦች ማሳወቅ።

**የስምምነት እና ፈቃድን የመሰረዝ መብት**

ለወደፊት ለሚደረጉ ማናቸውም የክፍል 2 ጤና መረጃ አጠቃቀሞች ወይም ይፋ የማድረግ ተግባራት ለሕክምና፣ ለክፍያ ወይም ለጤና እንክብካቤ የሥራ ማስኬጃ ዓላማዎች አንድ ወጥ የሆነ የጽሑፍ ስምምነት ሊሰጡ ይችላሉ (መረጃው እንዴት ጥቅም ላይ ሊውል እንደሚችል ከዚህ በታች በዝርዝር ቀርቧል)። Corewell Health በእርስዎ ስምምነት ላይ ተመስርቶ እርምጃ ከወሰደባቸው ተግባራት ውጭ፣ በፈለጉት ጊዜ የሰጡትን ስምምነት የመሰረዝ መብት አለዎት። ለሕክምና፣ ለክፍያ እና ለጤና እንክብካቤ የሥራ ማስኬጃ ተግባራት በታካሚው የጽሑፍ ስምምነት መሠረት ለክፍል 2 ፕሮግራም፣ ለሚመለከተው አካል ወይም ለሥራ አጋር የተገለጹ መዛግብት፤ የHIPAA ደንቦች እስከፈቀዱት ድረስ በክፍል 2 ፕሮግራም፣ በሚመለከተው አካል ወይም የንግድ አጋር አማካኝነት ያለ ታካሚው ተጨማሪ የጽሑፍ ስምምነት ለሌላ ወገን ሊገለጹ ይችላሉ።

**የጤና መረጃዎን እንዴት እንደምንጠቀም እና ግልጽ እንደምናደርግ**

**ለሕክምና፦** የጤና መረጃዎን ልንጠቀምበት እና እርስዎን ለሚያክሙ ሌሎች ባለሙያዎች ልንገልጽ እንችላለን። ለምሳሌ፦ በመጎዳትዎ ምክንያት የሚያክምዎ ሃኪም ከሌላ የጤና ህክምና እንክብካቤ አቅራቢ ጋር ስለ

አጠቃላይ የጤና ሁኔታዎ በተመለከተ ይጠይቃል።

የጤና መረጃዎን ለህክምና እንክብካቤ ቀጣይነት ዓላማዎች ሲባል ግልጽ ልናደርግ እንችላለን። የተለያዩ የCorewell Health ክፍሎች እንደ መድኃኒት ማዘዣ፣ የላብራቶሪ ምርመራ፣ ኤክስሬይ ወይም ቴራፒ ያሉ እርስዎን የሚያስፈልጉ ጉዳዮችን ለማስተናገድ ወይም ሪፈራልን ለማመቻቸት መረጃዎን እርስ በእርስ ሊለዋወጡ ይችላሉ።

**ክፍያ ለመፈጸም፡-** በCorewell Health ለሚያገኙት ሕክምና እና አገልግሎት ሂሳብ ለመጠየቅ እና ከጤና ዕቅዶች ወይም ከሌሎች አካላት ክፍያ ለማግኘት የእርስዎን የጤና እና የጤና ነክ ያልሆኑ መረጃዎችን ልንጠቀም እና ልንገልጽ እንችላለን። ለምሳሌ፡- እርስዎን የተመለከተ መረጃ ለጤና እንክብካቤዎ ወይም አገልግሎቶችዎ ክፍያ እንዲከፍልልዎት ለማድረግ ለጤና መድን ዋስትና ወጪ እቅድዎ ልንሰጥ እንችላለን። የኢንሹራንስ ዕቅድዎ ለሕክምናው ሽፋን እንደሚሰጥ ለማረጋገጥ ወይም ቅድመ ፈቃድ ለማግኘት ስለሚወስዱት ሕክምና ለጤና ዕቅዱ ልናሳውቅ እንችላለን።

ለተወሰነ የጤና እንክብካቤ አይነት ወይም አገልግሎት ሙሉ ክፍያ ከከፈሉ እና የጤና ወጪ ዕቅድዎ ስለዚህ ህክምና አይነት ወይም አገልግሎት በተመለከተ መረጃ እንዲያገኝ እንደማይፈልጉ ከነገሩን ይህን መረጃ እንድንገልጽ በህግ ካልተገደድን በስተቀር ለጤና ወጪ ዕቅድዎ አንገልጽም።

**ለጤና እንክብካቤ የሥራ ማስኬጃ ተግባራት፡-** እንደ ሂሳብ አያያዝ፣ የካሳ ጥያቄዎችን ማስተናገድ ወይም የሠራተኞቻችንን ብቃት መገምገምን የመሰሉ የሥራ ማስኬጃ ተግባራትን ለማከናወን የጤና መረጃዎን ልንጠቀም እና ልንገልጽ እንችላለን። እነዚህ መረጃ አጠቃቀሞች እና መረጃ ግልጽ የማድረግ ሂደቶች የCorewell Healthን የስራ እንቅስቃሴዎች ለማከናወን እና ሁሉም ታካሚዎቻችን ጥራቱን የጠበቀ እንክብካቤ እንዲያገኙ ለማረጋገጥ አስፈላጊ ናቸው።

እኛ ጋር ያለውን የጤና መረጃ አፈጻጸማችንን ለማነጻጸር እና እንዴት የምናቀርባቸውን እንክብካቤና አገልግሎቶች ማሻሻል እንደምንችል ለመወሰን ከሌሎች ድርጅቶች የጤና መረጃ ጋር አንድ ላይ ልናጣምር እንችላለን።

**የአስተዳደር ኦዲቶች፣ የፋይናንስ ኦዲቶች እና የፕሮግራም ግምገማ፡-** ኦዲት ለሚያደርጉ አካላት መረጃን ላለመግለጽ በሚገቡት ስምምነት መሠረት መረጃዎን ለኦዲት እና ለግምገማ ሥራ ኃላፊነት ላለባቸው አካላት ልንገልጽ እንችላለን። ኦዲቶች በፌዴራል፣ በስቴት እና በአካባቢ መስተዳድር መሥሪያ ቤቶች፣ እንዲሁም በሦስተኛ ወገን ከፋዮች እና የጤና ዕቅዶች የሚደረጉ የጤና ሥርዓት ክትትሎችን እና የሲቪል መብቶች ሕግጋት መከበራቸውን ማረጋገጥን ያካትታሉ።

## የጤና መረጃዎን እንዴት መጠቀም እና ይፋ ማድረግ እንደምንችል – ልዩ ሁኔታዎች።

**ድንገተኛ ሕክምና፡-** ድንገተኛ የሕክምና ሁኔታ ሲያጋጥም፣ የሕክምና ባለሙያዎች ለአደጋው ምላሽ እንዲሰጡ ለመርዳት አስፈላጊ እስከሆነ ድረስ ብቻ ያለ እርስዎ የጽሑፍ ስምምነት ማንነትዎን የሚገልጽ መረጃ ልንሰጥ እንችላለን።

**የምክር ማስታወሻዎች እና ከፍተኛ ምስጢራዊነት ያላቸው መረጃዎች፡-** እንደ ሳይኮቴራፒ እና የአደንዛዥ ዕፅ ሱሰኝነት የምክር ማስታወሻዎች (በአማካሪው ለብቻቸው ተለይተው የሚቀመጡ ማስታወሻዎች)፣ የአእምሮ ጤና እና የዕድገት እክል አገልግሎቶች እና የተወሰኑ በሽታዎች ያሉ የጤና መረጃዎች ልዩ የግላዊነት ጥበቃ ይደረግላቸዋል። ጥብቅ የህክምና ሚስጥር መረጃዎትን የምንጠቀመው ወይም ግልጽ የምናደርገው በህግ በሚፈቀደው ወይም በሚጠየቀው መሰረት ወይም በእርስዎ የጽሁፍ ፍቃድ ብቻ ነው።

ይሁን እንጂ፣ የክፍል 2 የምክር ማስታወሻዎችን ያለ የጽሑፍ ፈቃድ ይፋ ልናደርጋቸው እንችላለን፣ ይህም (i) ማስታወሻውን ባዘጋጀው ባለሙያ ለሚሰጥ ሕክምና፣ (ii) ተማሪዎች፣ ሰልጣኞች ወይም በSUD ሕክምና ወይም በአእምሮ ጤና ፕሮግራሞች ውስጥ ያሉ ባለሙያዎች የሥልጠና ፕሮግራሞች፤ እና/ወይም (iii) በታካሚው አማካኝነት በCorewell Health ላይ ለሚቀርብ የሕግ ክርክር ራስን ለመከላከል እንዲረዳ።

**የሕዝብ ጤና ስጋቶች፡-** በሽታን፣ ጉዳትን ወይም አካል ጉዳተኝነትን ለመከላከል ወይም ለመቆጣጠር እንዲቻል የጤና መረጃን ለሕዝብ ጤና ተግባራት ይፋ ልናደርግ እንችላለን። የሚቀርበው መረጃ ማንነትን የማይገልጽ መሆን አለበት፤ ይህም ማለት መረጃው እርስዎን ለመለየት ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል የሚል ምክንያታዊ ግምት እንዳይኖር ተደርጎ መዘጋጀት ይኖርበታል።

**የገንዘብ ማሰባሰቢያ እንቅስቃሴዎች፡-** Corewell Health ለክፍል 2 ፕሮግራሙ ጥቅም ሲባል ገንዘብ ለማሰባሰብ መዝገቦችን ሊጠቀም ወይም ሊገልጽ የሚችለው እርስዎ፣ ታካሚው፣መጀመሪያ የገቢ ማሰባሰቢያ መልዕክቶችን ላለመቀበል ግልጽ እና የማያከራክር የሆነ ምርጫ የማድረግ ዕድል ሲሰጥዎት ብቻ ነው። ከተስማሙ፣ በCorewell Health ባለቤትነት ወይም ቁጥጥር ስር ባለው ፋውንዴሽን በኩል ለCorewell Health ተባባሪዎች ገንዘብ ለማሰባሰብ እርስዎን ለማግኘት የተወሰኑ የሕክምና ያልሆኑ መረጃዎችን ልንጠቀም እንችላለን።

**በተቋሙ ግቢ ውስጥ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፡-** በተቋሙ ግቢ ውስጥ ወይም በሠራተኞቻችን ላይ ከሚፈጸም ወንጀል፣ ወይም እንዲህ ዓይነቱን ወንጀል ለመፈጸም ከሚደረግ ዛቻ ጋር በቀጥታ የተያያዙ መረጃዎችን ለሕግ አስከባሪ መኮንኖች ልንገልጽ እንችላለን።

**የወንጀል ፍትሕ ሥርዓት፡-** በወንጀል ፍትሕ ሥርዓት (የዕፅ ሱሰኝነት ፍርድ ቤትን፣ የሙከራ ጊዜን (probation) ወይም በሁኔታ መፈታትን (parole) ጨምሮ) በግዴታ ሕክምና ላይ ከሆኑ እና እንደ ፍርድ ቤት፣ የሙከራ ጊዜ መኮንኖች፣ የይቅርታ መኮንኖች፣ አቃቤ ሕግ ወይም ሌሎች የሕግ አስከባሪ አካላት ላሉ የወንጀል ፍትሕ ሥርዓት አካላት መረጃ እንዲገለጽ የሚፈቅድ ስምምነት ከፈረሙ፣ የሰጡትን ስምምነት የመሰረዝ መብትዎ ውስን ሊሆን ይችላል፤ ይህም በሚፈርሙት ስምምነት ላይ በግልጽ መብራራት ይኖርበታል።

**ሕጋዊ ከለላዎች፡-** በእርስዎ ላይ በሚቀርቡ ማናቸውም ሲቪል፣ አስተዳደራዊ፣ ወንጀል ወይም የሕግ አውጪ ሂደቶች ላይ በእርስዎ የጽሑፍ ስምምነት ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ካልሆነ በስተቀር መዛግብት ወይም የመዛግብቱን ይዘት የሚገልጽ የምስክርነት ቃል ጥቅም ላይ ሊውሉ ወይም ይፋ ሊደረጉ አይችሉም። መዛግብት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሠረት ጥቅም ላይ ሊውሉ ወይም ይፋ ሊደረጉ የሚችሉት በ42 USC § 290dd-2 እና 42 CFR የክፍል 2 መሠረት ለታካሚው እና/ወይም ለመዝገቡ ያዡ ማስታወቂያ ከተሰጠ እና የመሰማት ዕድል ካገኘ በኋላ ብቻ ነው። መረጃውን ለመጠቀም ወይም ይፋ ለማድረግ የሚሰጥ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ፣ መረጃው ጥቅም ላይ ከመዋሉ ወይም ይፋ ከመደረጉ በፊት መረጃው እንዲገለጽ የሚያስገድድ የፍርድ ቤት መጥሪያ (subpoena) ወይም ሌላ ተመሳሳይ የሕግ ትዕዛዝ

አብሮት ሊቀርብ ይገባል።

**ምርምር፦** የተወሰኑ መስፈርቶች ከተሟሉ መረጃዎን ለምርምር ልንጠቀምበት እና ይፋ ልናደርግ እንችላለን።

**የተጠረጠሩ የህፃናት ጥቃት እና ትኩረት ማጣት ሪፖርቶች፦**
በክልል ሕግ መሠረት የሕፃናት ጥቃት እና ትኩረት ማጣት ክስተቶችን ለሚመለከተው የክልል ወይም የአካባቢ ባለስልጣናት ሪፖርት ለማድረግ የሚያስፈልገውን መረጃ ይፋ ልናደርግ እንችላለን። ይሁን እንጂ፣ ያለፈቃድ በልጆች ጥቃት እና ትኩረት ማጣት ከተጠረጠረው ሪፖርት ሊነሱ የሚችሉትን የፍትሐ ብሔር ወይም የወንጀል ሂደቶችን ጨምሮ የመጀመሪያዎቹን የታካሚ መዝገቦች ይፋ ላናደርግ እንችላለን።

**ሞትን ሪፖርት ማድረግ፦** ከሞት መንስኤ ጋር የተያያዘ መረጃዎን እንዲህ ዓይነቱን መረጃ እንዲቀበል ሥልጣን ላለው የሕዝብ ጤና ባለሥልጣን ልንገልጽ እንችላለን።

**ሌሎች የእርስዎ የጤና መረጃ አጠቃቀሞች፦** በዚህ ማስታወቂያ ወይም በCorewell Health ላይ ተፈጻሚ በሚሆኑ ሕጎች ያልተሸፈኑ ሌሎች የጤና መረጃ አጠቃቀሞች እና ይፋ የማድረግ ተግባራት የሚከናወኑት በእርስዎ የጽሑፍ ፈቃድ ብቻ ነው። የህክምና መረጃዎን እንድንጠቀም ወይም እንድንገልጽ ፍቃድ ከሰጡን ፍቃዱን በየትኛውም ጊዜ በጽሁፍ መሻር ይችላሉ። ፍቃድዎን የሚሽሩ ከሆነ እርስዎን የተመለከተ የጤና መረጃዎን በጽሁፍ ፍቃድዎ ስር በተካተቱ ምክንያቶች አንጠቀምም ወይም ግልጽ አናደርግም። ሆኖም፣ በእርስዎ ፈቃድ ቀደም ብለን ያከናወናቸውን ተግባራት ወደ ኋላ መመለስ አንችልም፤ እንዲሁም ለሰጠናችሁ እንክብካቤ ያዘጋጀናቸውን መዛግብት የመያዝ ግዴታ አለብን።

**ከጤና መረጃዎ ጋር በተያያዘ ያሉዎት መብቶች**
**የመመርመር እና የመቅዳት መብት፦** የእርስዎን የሕክምና መዝገብ እና ስለ እርስዎ ያሉንን ሌሎች የጤና መረጃዎች ለማየት ወይም በኤሌክትሮኒክ ወይም በወረቀት ቅጂ ለማግኘት መጠየቅ ይችላሉ። ለእርስዎ የሚቀርበው መረጃ የሕክምና እና የክፍያ መዛግብትን ያካትታል፤ ነገር ግን የሳይኮቴራፒ ማስታወሻዎችን አይጨምርም። የጤና መረጃዎን ኮፒ ወይም ማጠቃለያ በአብዛኛው ጥያቄ ባቀረቡልን በ30 ቀናት ውስጥ እንሰጥዎታለን። ምክንያታዊ፣ ወጪን መሰረት ያደረገ ክፍያ ልናስከፍል እንችላለን። በጥቂት በጣም ውስን ሁኔታዎች መረጃን የማየት እና የመቅዳት ጥያቄዎን ውድቅ ልናደርግ እንችላለን። መረጃ የማግኘት ጥያቄዎ ውድቅ ከተደረገ፣ ውሳኔው እንደገና እንዲታይ መጠየቅ ይችላሉ። በCorewell Health የሚመረጥ ሌላ ፍቃድ የተሰጠው የጤና እንክብካቤ ባለሙያ ጥያቄዎትን እና ክልከላውን ይመረምራል። ግምገማውን የሚያካሂደው አካል መጀመሪያ ጥያቄዎን ውድቅ ያደረገው ግለሰብ መሆን የለበትም። በግምገማው ውጤት መሠረት እንፈጽማለን። በምርምር ሥራዎች ላይ እየተሳተፉ ከሆነ፣ ከመሳተፍዎ በፊት በፈረሙት የፈቃድ ቅጽ ላይ መረጃ የማየት ገደቡን ከተስማሙ፣ ከምርምሩ ጋር የተያያዙ የተወሰኑ የጤና መረጃዎችዎን የማየት እና የመቅዳት ጥያቄን ውድቅ ልናደርግ እንችላለን። እንዲሁም በሕግ በተፈቀደው መሠረት መረጃ የማግኘት ጥያቄን ውድቅ ልናደርግ እንችላለን።

**የማሻሻል መብት፦** ስለ እርስዎ የተመዘገበ የጤና መረጃ ስህተት ነው ወይም አልተሟላም ብለው ካሰቡ፣ የጤና መረጃ አያያዝ ክፍል (Health Information Management Department) እንዲያስተካክልልዎ መጠየቅ ይችላሉ። ጥያቄዎ "ውድቅ ሆኗል" ልንልዎ እንችላለን፣ ሆኖም ለምን ለምን ውድቅ እንዳደረግነው በ60 ቀናት ውስጥ በጽሁፍ እናሳውቅዎታለን። የማሻሻል ጥያቄዎን በጽሁፍ ካልቀረበ ወይም ጥያቄውን የሚደግፍ ምክንያት ካላካተተበት ውድቅ ልናደርገው እንችላለን። እንዲሁም የሚከተሉትን መረጃዎች እንዲሻሻሉ ከጠየቁ ውድቅ ልናደርግ እንችላለን፦

- መረጃውን የፈጠረው ሰው ወይም ተቋም ማሻሻያውን ለማድረግ ከእንግዲህ በኋላ የማይገኝ ካልሆነ በስተቀር በእኛ አልተፈጠረም።
- በCorewell Health ወይም ለCorewell Health ተብለው ከሚያዙ የጤና መረጃዎች ወገን ካልሆነ።
- እርስዎ እንዲያዩት እና እንዲቀዱት ከሚፈቀድልዎ መረጃዎች ወገን ካልሆነ።
- መረጃው ትክክለኛ እና የተሟላ ከሆነ።

**ይፋ የተደረጉ መረጃዎች ዝርዝር የማግኘት መብት** ጥያቄ ካቀረቡበት ቀን ጀምሮ ባሉት ባለፉት ሦስት ዓመታት ውስጥ የእርስዎን የጤና መረጃ ለማን እንዳጋራን እና ለምን ዓላማ እንደተጋራ የሚገልጽ ዝርዝር (accounting) እንዲሰጥዎ መጠየቅ ይችላሉ። ይህንን ዝርዝር እንዴት መጠየቅ እንደሚችሉ የጤና መረጃ አያያዝ ክፍልን (Health Information Management Department) ይጠይቁ። ዝርዝሩ ለሕክምና፣ ለክፍያ እና ለሥራ ማስኬጃ ተግባራት የተደረጉ መገለጫዎችን፣ እንዲሁም የተወሰኑ ሌሎች መገለጫዎችን (ለምሳሌ እርስዎ እንዲደረጉ የጠየቁትን) አያካትትም። በዓመት አንድ ጊዜ ዝርዝሩን በነፃ እንሰጥዎታለን፤ ነገር ግን በ12 ወራት ውስጥ ሌላ ተጨማሪ ዝርዝር ከጠየቁ ምክንያታዊ የሆነ የወጪ መሸፈኛ ክፍያ ልንጠይቅ እንችላለን። ጥያቄዎ ዝርዝሩን በምን ዓይነት ቅርጸት (ለምሳሌ በወረቀት ወይም በኤሌክትሮኒክ) ማግኘት እንደሚፈልጉ መግለጽ አለበት።

**ገደቦች እንዲጣሉ የመጠየቅ መብት፦** የተወሰኑ የጤና መረጃዎች ለሕክምና፣ ለክፍያ ወይም ለሥራ ማስኬጃ ተግባሮቻችን ጥቅም ላይ እንዳይውሉ ወይም ይፋ እንዳይደረጉ የመጠየቅ መብት አለዎት። ሙሉ የአገልግሎት ወይም የጤና እንክብካቤ ክፍያዎን ከኪስ አውጥተው (በእራስዎ ወጪ) ከከፈሉ ይህን መረጃ ለጤና መድን ዋስትና ሰጪዎ ግልጽ እንዳናደርግ ሊጠይቁን ይችላሉ። መረጃውን እንድንገልጽ ህግ ካላስገደደን፣ በእንክብካቤዎ ላይ ተጽእኖ የሚፈጥር ካልሆነ ወይም ጥያቄዎን ማክበር ካልቻልን በስተቀር "እሺ" እንልዎታለን።

**ሚስጥራዊ ግንኙነቶችን የመጠየቅ መብት፦** ስለ ጤና እንክብካቤ ጉዳዮች በተወሰነ መንገድ ወይም በተወሰነ ቦታ ላይ ከእርስዎ ጋር እንድናነጋግርዎ መጠየቅ ይችላሉ። ለምሳሌ፦ በስራ ቦታዎ ላይ እያሉ ወይም በኢሜይል ብቻ ከእርስዎ ጋር ግንኙነት እንድናደርግ ሊጠይቁን ይችላሉ። በሁሉም አሳማኝ በሆኑ ጥያቄዎች እንስማማለን። ጥያቄውን በምዝገባ ወቅት፣ ለታካሚ ወኪልዎ ወይም ለግላዊነት ቢሮው ማቅረብ ይችላሉ። ጥያቄዎን በጽሁፍ እንዲያቀርቡ ልንጠይቅዎ እንችላለን።

**ቅሬታ ማቅረብ**
የግላዊነት መብቶቼ ተጥሰዋል ብለው ካመኑ፣ ለU.S. Department of Health and Human Services ጸሐፊ (Secretary) እና ለCorewell Health ቅሬታ የማቅረብ መብት አለዎት። ጥሰቱን ለጸሐፊው ወይም ለCorewell Health ሪፖርት የማድረግ ግዴታ የለብዎትም፤ ነገር ግን ለሁለቱም ወይም ለአንዱ ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ። ቅሬታ በማቅረብዎ ምክንያት ምንም ዓይነት ቅጣት ወይም የአጸፋ እርምጃ አይወሰድብዎትም።

ለአሜሪካ የጤና እና የሰብዓዊ አገልግሎቶች መሥሪያ ቤት የሰብዓዊ መብቶች መምሪያ (U.S. Department of Health and Human Services Office for Civil Rights) ቅሬታ ለማቅረብ **ocrportal.hhs.gov/ocr/smartscreen/main.jsf** ን ይጠቀሙ።

ለCorewell Health ቅሬታ ለማቅረብ በነፃ የስልክ መስመር
**877.319.0266** በመደወል፣ **privacy@corewellhealth.org**
ኢሜይል በመላክ ወይም በጽሁፍ ለሚከተለው አድራሻ ማቅረብ ይችላሉ፦

Corewell Health
ATTN: Chief Privacy Officer MC6481
100 Corewell Drive NW
Grand Rapids, MI 49503

**በዚህ ማስታወቂያ ላይ የሚደረጉ ለውጦች**

በዚህ ማስታወቂያ ላይ ለውጥ የማድረግ መብታችን የተጠበቀ ነው። እንዲሁም የተሻሻለው ማስታወቂያ ቀደም ሲል ስለ እርስዎ ባለን የጤና መረጃ እና ወደፊት በምናገኘው ማንኛውም መረጃ ላይ ተፈጻሚ እንዲሆን የማድረግ መብታችን የተጠበቀ ነው። የአሁኑን ማስታወቂያ ኮፒ በተቋሞቻችን፣ ቢሮዎቻችን እና ማስታወቂያው በሚሸፍናቸው ቦታዎች ላይ እንለጥፋለን። ማስታወቂያው ተፈጻሚ የሚሆንበትን ቀን ይይዛል። በተጨማሪም፣ በክፍል 2 ተቋም ወይም ቢሮ በተመዘገቡ ቁጥር ወይም እንደ ታካሚ ወይም ተመላላሽ ታካሚ ሆነው ለህክምና ወይም ለጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች ወደ ክፍል 2 ተቋም ሲገቡ፣ የቅርብ ጊዜውን የማስታወቂያ ቅጂ ለእርስዎ ይቀርብልዎታል።